## ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

### ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ተቋማዊ የሴቶች አደረጃጀት- ለተሳትፎና ተጠቃሚነት

ሀገራት የባህላዊ አስተሳሰብ ተጽዕኖዎችንከሴቶች ጫንቃ ላይ እያወረዱ ፤ ሴቶች በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ከወንዶች ባልተናነሰ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ እየቀየሱ ይገኛል። ከዚህ አንጻር ገና መሠራት የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም አንዳንድ አበረታች ጅምሮችን እያስተዋልን መሆኑ የሚበረታታ ነው።

በኢትዮጵያ በተለይም በቅርቡ ከተደረገው ለውጥ ወዲህ ሴቶች እና ወንዶች ሃምሳ ሃምሳ በመቶ ድርሻ ተሰጥቷቸው ለከፍተኛ አመራርነት ሲታጩ ተመልክተናል። ምንም እንኳን በታችኞቹ እርከኖች ገና ብዙ መሥራትን የሚጠይቅ እንደሆነ ቢታመንም በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ የሴቶችን ስብጥር ከወንዶች ጋር ለማመጣጠን የሚሠሩ ሥራዎች እንዳሉ ይታወቃል። አጠቃላይ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በየተቋሙ የሴቶች፣ ሕጻናትና ወጣቶች ዘርፍ ተቋቁሞ በንቃት እየሠራ መሆኑንም ተመልክተናል።

ወይዘሮ ሌንሴ ኢዳኤ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሴቶች ሕጻናትና ወጣቶች መምሪያ ዳይሬክተር ናቸው። በተቋሙ ስለሚከናውኑት ሥራዎች እንዲህ ያስረዳሉ። የሥራ ክፍሉ በዋናነት በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ ግንዛቤ በማስጨበጥ የፆታ እኩልነት እንዲመጣ የማስቻልእና የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ሥራዎችን ይሠራል። እንዲህ አይነት አስቻይ ሥራዎች ከመሠራታቸው በፊት በተቋም ደረጃ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችሉ መመሪያዎችና ደንቦችም ይዘጋጃሉ።

እንደተቋም የሴቶች ቁጥር አነስተኛ መሆኑን የተናገሩት ዳይሬክተሯ፤ ለዚህ ምክንያቱ አብዛኛው ሥራ ከምህንድስና ጋር የተያያዘና ከዩኒቨርሲቲ ጀምሮ በዚህ ዘርፍ የሚመረቁ ሴት ተማሪዎች ቁጥር አናሳ መሆንን እንደ አንድ ምክንያት ያስቀምጣሉ። አብዛኛዎቹ



ወይዘሮ ሌንሴ ኢዳኤ

ሥራዎች መስክ የሚያስወጡ፣ ተራራ መውጣትና መውረድን የሚጠይቁ፣ የብረት ማማዎች ላይ ወጥቶ መሥራትን የሚፈልጉ፣ ከከተማ ውጪ በካምፕ ውስጥ መኖርን የሚያስገድዱ እና ሌሎችም ፈታኝ ሁኔታዎች ያሏቸው መሆኑ የተመረቁት ጥቂት ቁጥር ያላቸው መሃንዲሶችም ተቋሙን የመቀላቀል ድፍረት እንዳያገኙ አድርጓቸዋል ይላሉ። ተቋሙ በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ ካሉት ስምንት ሺህ ቋሚና ጊዜያዊ ሠራተኞች ውስጥ 15 በመቶ ሴት ሠራተኞች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ከእነዚህ ውስጥ በአመራር ደረጃ ያሉት አስራ አንድ በመቶ ብቻ እንደሆኑ ተናግረዋል።

ሴቶች ከሀገሪቱ አጠቃላይ ሕዝብ ቁጥር አንጻር ሃምሳ በመቶ ድርሻ እንዳላቸው የተናገሩት ዳይሬክተሯ፤ በዚህ ትልቅ ተቋም ውስጥ ግን ምጣኔው በሚጠበቀው ልክ እንዳልሆነ ተናግረዋል። በተቋሙ የሴቶችን ቁጥርም ይሁን በአመራር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ገና ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስምረውበታል።

በዋናነት ግን ችግሩን መቅረፍ የሚቻለው በተቋሙ ውስጥ በሚሠራ ሥራ ብቻ ሳይሆን ከትምህርት ቤት ጀምሮ በሚሠራ ሥራ እንደሆነ አስረድተዋል። ችግሩን ከምንጩ ለማስወገድ ትምህርት ቤቶች የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ አሠራሮችን ሊከተሉ ይገባል ይላሉ።

በተቋሙ የሚስተዋለውን የምጣኔ ችግር ለማስተካከል ቅጥር ሲፈጸም 30 በመቶ ለሴቶች ልዩ ድጋፍ የሚደረግበት አሠራር እንዳለ የተናገሩት ወይዘሮ ሌንሴ፤ በበጀት ዓመቱ ወደ ተቋሙ ከተቀላቀሉ 100 አዳዲስ ሠራተኞች ውስጥ 33ቱ ሴት መሃንዲሶች መሆናቸውን አስረድተዋል።

በተጨማሪም የተቋሙን ሴት ሠራተኞች ወደ አመራርነት ለማምጣት የሚያስችል ስልጠና መስጠቱንም አስታውሰዋል። ለነባር እና አዳዲስ የተቋሙ ሴት ሠራተኞች በመሪነት ሚና ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችላቸውን ዝግጅት ከወዲሁ እንዲያደርጉ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ መሠራቱን አስረድተዋል።

የእናቶችን ጫና ለመቀነስ በዋናው መሥሪያ ቤት ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ በመምሪያው ስር የሚተዳደር የሕጻናት ማቆያ ማዕከል እንደተዘጋጀ የተናገሩት ወይዘሮ ሌንሴ፤ ይህም እናቶች ልጆቻቸውን በቅርበት እየተከታተሉ ሥራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል ይላሉ። በአሁኑ ወቅት 29 የሚሆኑ ሕጻናት ስምንት ሞግዚቶችና አንድ የጤና ባለሙያ (ነርስ) ተመድበውላቸው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው። ማዕከሉ በመከፈቱ ለዘጠኝ ሰዎች የሥራ እድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

ማዕከሉ ሥራ ከጀመረ ወዲህ በተለይም ለእናቶች እፎይታን የፈጠረ እንደሆነ ገልጸዋል። እናቶች በቤት ሠራተኞች አማካኝነት ልጆቻቸው ላይ የሚፈጸም አደጋ ይኖራል የሚል ስጋት እንዳይኖራቸውና በአንድ ልብ ሆነው ሥራቸውን እንዲያከናውኑ አስፈላጊም ሲሆን በእረፍት ሰዓታቸው ልጆቻቸውን እንዲያጠቡ አስችሏቸዋል። ተቋሙ ለእናቶች እያደረገላቸው ባለው እገዛ በጣም ደስተኛ መሆናቸውን በሰጡት ምላሽ መረጋገጥ እንደተቻለ ወይዘሮ ሌንሴ ገልጸዋል። የማርፈድና ከሥራ ገበታ የመቅረት መጠንም ቀንሷል። ከወለዱ በኋላ ልጆቻቸውን ጡት ለማጥባት በሚል ያለ እቅዳቸው የዓመት እረፍት የሚወስዱ እናቶች ከሥራ ሳይቀሩ ልጆቻቸውን እንዲንከባከቡ አስችሏል። ይህ መሆኑ በድርጅቱ ሥራ ውጤታማነት ላይ እራሱን የቻለ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነ ተናግረዋል።

በዚህ አዲስ ባህል እናቶች ዘመናዊ የልጅ አስተዳደግ ሥርዓትን እየተላመዱ እንዲሄዱ፣ ከሕጻናት አመጋገብና አያያዝ እንዲሁም ከዕለት ተዕለት የጤና ክትትል አንጻርም ከጤና ባለሙያዎችና ከሞግዚቶች የሚያገኙት ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ አንዷ እናት ከሌላዋ እናት የልምድ ልውውጥ እንድታደርግ እድል የፈጠረነው። ማዕከሉ ለሕጻናት ከሚያደርገው እንክብካቤ በተጨማሪ እናቶች በዘለቄታው ልጆቻቸውን እንዴት መንከባከብ እንደሚገባቸው ለሁለት ጊዜ ያህል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል።

እስከ አሁን ለሕጻናት የሚሰጠው አገልግሎት በቤት ውስጥ ብቻ ተወስኖ እንዳለ የተናገሩት ዳይሬክተሯ፤ በቀጣይ ከቤት ውጪ የሕጻናት መጫወጫዎችን ያካተተ ቦታ ለማዘጋጀት ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ይገኛሉ ብለዋል። እንዳስፈላጊነቱ የሕፃናት ማቆያ ማዕከላትን በተለያዩ ማዕከላትና ኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ለማስፋፋት መታሰቡን የተናገሩት ወይዘሮ ሌንሴ፤ በቅርቡ በአዳማ-1 የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ለማስጀመር አስፈላጊ የተባሉ ግብዓቶች እየተሟሉ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል